# አዋጅ ቁጥር---/2014

## የኢትየጵያ ዲጂታል መታወቂያ አዋጅ

በኢትዮጵያ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት መዘርጋት ነዋሪዎች የመታወቅ መብታቸው እንዲረጋገጥ፣ ሌሎች መብቶችን የመጠቀም እድሎችን ለማስፋት፣ የአገልግሎት ሰጪና ተቀባይ መካከል በሚኖር ግንኙነት ላይ እምነት እንዲዳብር ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የግልጽነት ፣ የተጠያቂነት እና የተሳለጠ አሠራር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል በመሆኑ ፤

በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የበለፀገ ፣ ዘርፍ ተሻጋሪ ፣ መሠረታዊ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት መዘርጋት ፤ ሃገራዊ ልማትን በአግባቡ ለማቀድ ፣ ምጣኔ ሃብታዊ ሽግግር ለመፍጠር ፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ፣ የሀብት ብክነትን ለመቀነስ፣ ፖሊሲዎች ሲቀረጹ እና የልማት ሥራዎች ሲከናወኑ ድግግሞሽን ለመቅረፍ አካታችነትን ለማጎልበት፣ እና በነዋሪዎች መካከል ፍትሀዊ የሃብት ክፍፍል ለማስፈን የሚረዳ በመሆኑ፤

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በሐገር አቀፍ ደረጃ በመዘርጋት፣ አስተማማኝ ፥ ተደራሽ እና ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ሥርዓትን ማጎልበት ፣ የሐገሪቱን ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እና ተገማችነትን ለማሳደግ ፤ የነዋሪዎችን ሁለንተናዊ ሰላምና ደህንነትን ለማረጋገጥና የፍትህ ሥርዓቱን ለማጠናከር የሚረዳ በመሆኑ፤

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በሃገሪቱ ባለመኖሩ፣ ለመንግሥትም ሆነ ለግል ተቋማት አንድን ነዋሪ በልዩ እና በአስተማማኝ ሁኔታ ለመለየት አስቸጋሪ በመሆኑ፤ በሀገሪቱ የሚገኙ ነዋሪዎች ራሳቸውን በቀላሉ ማስታወቅ የሚችሉበትና አገልግሎት የሚያገኙበት ወጥ የመታወቂያ ሥርዓት ባለመኖሩ ፣ በተጨማሪም አስተማማኝ የሆነ የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት አለመኖር አገራዊም ሆነ ክልላዊ የልማት ፖሊሲዎችን ለመቅረፅ አዳጋች መሆንና፣ በአገልግሎት አሰጣጥ እና በመልካም አስተዳደር ላይ እንቅፋት እየፈጠረ በመሆኑ እና እነዚህን ችግሮች በህግ ማእቀፍ መቅረፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

ሁሉን አቀፍ ፣ ወጥና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ የሐገሪቱ ነዋሪዎች የሚመዘገቡበትን ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በመዘርጋት እና የተመዝጋቢዎችን መረጃ በመያዝ የዲጂታል መታወቂያ አጠቃቀም ሥርዓትን ሕጋዊ መሠረት እንዲኖረው ለማድረግ፤ በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓቱ ውስጥ ባሉ የተለያዩ አካላት ማለትም ተመዝጋቢ፣ መዝጋቢ፣ ተጠቃሚ አካላት ፣ አረጋጋጭ አካላት እና በዲጂታል መታወቂያ ተቋም መካከል የሚኖረውን ግንኙነት በሕግ የሚመራበትን የመተማመኛ ማዕቀፍ መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “**የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ቁጥር...../2014**” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ “***መሠረታዊ መታወቂያ***” ማለት በአንድ ነዋሪ ልዩ ማንነት ላይ በመመስረት አገልግሎቶችን በቀላሉ ማግኘት ይችል ዘንድ የሚረዳ ሕጋዊ መለያ ነው፤

2/ “**የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት**” ማለት የዲሞግራፊክ እና ባዮሜትሪክ መረጃ መዝግቦ በማዕከላዊ ቋት በመያዝና ለእያንዳንዱ ነዋሪ ልዩ ቁጥር በመሥጠት የተደራጀ እና አስተማማኝ መሠረታዊ የመታወቂያ ሥርዓት ነው፤

3/ “**ዲጂታል መታወቂያ**” ማለት በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ውስጥ ለተመዘገበ ነዋሪ የሚሰጥ መለያ ሲሆን በልዩ ቁጥሩ በኩል የመሠረታዊ መታወቂያ አገልግሎት ይሰጣል፤

4/ “**የህፃናት ዲጂታል መታወቂያ**” ማለት ዕድሜው በዲጂታል መታወቂያ ተቋም ከተወሰነው ዓመት በታች ለሆነና ለአካለ መጠን ላልደረሰ ህፃን ያለ ባዮሜትሪክ መረጃ የሚሰጥ ልዩ ቁጥር ያለው ጊዜያዊ የዲጂታል መታወቂያ ዓይነት ነው፤

5/ **“ባዮሜትሪክ መረጃ”** ማለት  የጣት አሻራ፣ የዐይን ብሌንና የፊት ገፅታ ምስልን በስሌት ለመያዝ የሚቻሉ የአንድ የተፈጥሮ ሰው ልዩ የሰውነት አካላዊ መለያዎች ናቸው፤

6/ **“የዲሞግራፊክ መረጃ”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተጠቀሱት ወደ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የሚገቡ የተመዝጋቢ መረጃዎች ሲሆኑ የባዮሜትሪክ መረጃን አይጨምርም፤

7/ **“ልዩ ቁጥር”** ማለት በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ውስጥ አንድ ነዋሪ ስኬታማ ምዝገባ ሲያጠናቅቅ ለተመዝጋቢ የሚሰጥ ልዩ፣ ተደጋጋሚ ያልሆነ ቁጥር ሲሆን ፤ በልዩ ሁኔታ ተቋሙ በሚሰጠው ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር ፤ አንዴ ለተመዝጋቢ ከተሰጠ የማይለወጥ ቋሚ ቁጥር ነው፤

8/ **“ተለዋጭ ቁጥር’’** ማለት ከዲጂታል መታወቂያ ጋር በሚስጥራዊ ሁኔታ የተያያዘ ፤ የተመዝጋቢን ግላዊነት ለመጠበቅ በሚያስችል መልኩ ከዲጂታል መታወቂያ ሥርዓቱ አንድም ሆነ ከዛ በላይ ሊፈጠር የሚችል ልዩ ቁጥር ነው፤

9/ **‘’ተቋም’’** ማለት የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓትን የሚያስተገብርና ይህንን አዋጅ የሚያስፈጽም መንግሥታዊ የዲጂታል መታወቂያ ተቋም ነው፤

10/ **“ነዋሪ”** ማለት በሃገሪቱ ውስጥ የሚኖር የተፈጥሮ ሰው ሲሆን ፤ ዜጋም ሆነ ዜግነቱ ያልተረጋገጠ እንዲሁምበህግ ፈቃድ አግኝቶ የሚኖር ወይም የሚሠራ ሰውን ይጨምራል፤

11/**“ተመዝጋቢ”** ማለት የዲሞግራፊክ እና የባዮሜትሪክ መረጃ በመስጠት፣ ምዝገባ አከናውኖ የዲጂታል መታወቂያ የሚሰጠው ነዋሪ የሆነ ሰው ነው፤

12/ **“መዝጋቢ አካል”** ማለት የዲጂታል መታወቂያ ተቋም ወይም በተቋሙ በሚሰጥ ፈቃድ ወይም ውክልና መሠረት የተመዝጋቢን መረጃ የሚሰበስብ አካል ነው፤

13/ **“ምዝገባ”** ማለት ከመዝጋቢ አካል ወደ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓቱ የተላከ የተመዝጋቢ መረጃን ልዩ በሆነ ሁኔታ በማረጋገጥ የመመዝገብ ሂደት ነው።

14/ **“ተጠቃሚ አካል”** ማለት ከዲጂታል መታወቂያ ተቋም እና ከግለሰቡ በተሰጠ ፈቃድ እና መረጃ ላይ ተመስርቶ የግለሰብ ማንነትን የሚያረጋገጥ አካል ነው፤

15/ **“ማረጋገጥ**" ማለት ከዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ማእከላዊ መረጃ ቋት ጋር ቀጥታ በኔትወርክ ወይም ያለኔትዎርክ በማመሳከር የግለሰብን ማንነት የማጣራትና ማረጋገጫ የመስጠት ሂደት ነው።

16/ **“አረጋጋጭ አካል**" ማለት የዲጂታል መታወቂያ መረጃዎች ከተጠቃሚ አካል በሚቀርብ ጥያቄ የማረጋገጥ አገልግሎት የሚሰጥ አካል ነው፤

17/ **“የግል መረጃ”** ማለት የባዮሜትሪክ መረጃን ጨምሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተጠቀሱት ወደ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ማለት ነው፤

18/“**ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል መረጃ**” ማለት:-

ሀ) ዘርን ወይም ብሔርን፣

ለ) የዘረመል ፤

ሐ) የአካላዊ ወይም የአዕምሯዊ ጤንነት ወይም ሁኔታን፣

መ) የወሲባዊ ሕይወትን፣

ሠ) የፖለቲካ አመለካከትን፣

ረ) ሃይማኖትን ወይም ሌላ ሃይማኖት ነክ አስተሳሰብን፣

ሰ) የተፈጸመ ወይም ተፈጸመ የተባለ ወንጀልን፤

ሸ) የተፈጸመ ወይም ተፈጸመ የተባለ ወንጀልን አስመልክቶ የተካሄዱ ሂደቶችን፣ እነዚህ ሂደቶች የተጠናቀቁበት መደምደሚያን ወይም በሂደቶቹ ዙሪያ ፍርድ ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሳኔን፣

(ቀ) በተቋሙ ወይም ሌሎች ሥልጣን ባላቸው ተቋማት የሚወሰኑ ጥንቃቄ የሚፈልጉ የግል መረጃዎችን ሊጨምር ይችላል፤

19/"**ፈቃድ**" ማለት አንድ ተመዝጋቢ የግል መረጃውን ግልጽ ለሆነ ዓላማ እንዲቀናበር በጽሁፍ፣ በቃል፣ በዲጂታል ወይም በማናቸውም ጥርጣሬ በማያስነሳ ሁኔታ የሚሰጠው ስምምነት ነው፤

20/“የዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ” ማለት ልዩ የመታወቂያ ቁጥር ወይም ተለዋጭ ቁጥርና የተመዝጋቢ መረጃ የያዘ በቁሳዊ ወይም በዲጂታል አማራጭ የሚዘጋጅ የሰነድ ማስረጃ ነው፤

21/**“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ፥ ለዚህ አዋጅ ዓላማ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

22/**“መንግሥት”** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሲሆን ለዚህ አዋጅ ዓላማ የክልሎች አስተዳደሮችንም ያካትታል፤

23/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ሰው ማለት ነው፤

24/ በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ኢትዮጲያ ውስጥ በሚገኝ በማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 4. የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ተቋም

1/ በዚህ አዋጅ መሠረት የዲጂታል መታወቂያን ስርዓት በተመለከተ የተደነገጉ ተግባርና ኃላፊነቶችን የሚያስፈፅም ተቋም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይቋቋማል፤

2/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ፤ ተቋሙ የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነቶች ይፈፅማል፡-

ሀ) የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የማናቸውንም ነዋሪ ማንነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የመሠረታዊ መታወቂያ ሆኖ በሚያገለግለበት አግባብ ማደራጀት፣

ለ) የመሠረታዊ መታወቂያ አገልግሎትን ለመስጠት የሚያገለግሉ የባዮሜትሪክ መረጃዎችን የመሰብሰብ ወይም ለሌሎች ፍቃድ መስጠት፣

ሐ) የዲጂታል መታወቂያ ስርዓትን በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ለሚሰጡ የግለሰብ መታወቂያ ካርዶች እና ሌሎች ለተፈቀደላቸው አገልግሎት ሰጪዎች መሠረት በመሆን እንዲያገለግል አድርጎ የማደራጀት፣

መ) ለነዋሪዎች የግል መረጃ ትክክለኛነት፣ ደህንነት እና ጥበቃ ሲባል በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ውስጥ ያለው መረጃ በዚህ አዋጅ ለተገለጸው ዓላማ ብቻ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል የአሠራር ስርዓት መዘርጋት፣

ሠ)ለፖሊሲ እና ለመንግስት ለአመራር ውሳኔ ለመስጠት በሚያመች መልኩ የዲሞግራፊክ መረጃ ስርዓት በመዘርጋት ፣በሀገሪቱ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦችን መረጃ አደራጅቶ ለመያዝ በሚያስችል መልኩ አሠራር መዘርጋት፣

ረ) ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሴክተሮች አስፈላጊ የሆኑ የማረጋገጥ አገልግሎቶችን ፣ በመስጠት አረጋጋጭ አካል ሆኖ ማገልገል፣

ሰ) የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ተገቢነት ያለው የአስተዳደር እና የገቢ መዋቅር እንደአስፈላጊነቱ መዘርጋት፣

ሸ) ከሚመለከታቸው አካላትና የዲጂታል ስርዓቶች ጋር በመቀናጀት ፣ መረጃ የማጋራትና የመለዋወጥአገልግሎት ይሰጣል ፣

ቀ)በባዮሜትሪክስ እና ተዛማጅ ዘርፎች በተለይም የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓቱ ላይ የምርምርና የልማት ሥራዎችን እንዲጎለብቱ ማድረግ፣

## ክፍል ሁለት
## ስለ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት መርሆዎች ፣ ምዝገባ እና አገልግሎት አሰጣጥ

## 5. መርሆዎች

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል፡-

1/ ሁሉን አቀፍ ፣ ከአድሏዊ አሠራር ነፃ የሆነ ፣ ተደራሽ እና ለአጠቃቀም ምቹ የሆነ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት መዘርጋት አለበት፤

2/ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የሚታመን ፤ ከሥርዓቱ ንድፍ ጀምሮ ግላዊነት እና ደህንነቱ የተጠበቀ ፣ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ ፤ ሴክተር እና ድንበር ተሻጋሪ ሆኖ ከሌሎች ሥርዓቶች ጋር መናበብ የሚችል ፤ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ሉአላዊነትን የሚያረጋግጥ እንዲሁም ዘላቂ የፋይናንስ እና የክወና ዕቅድ ያለው መሆን አለበት፤

3/ የግል መረጃ ደህንነት እና ጥበቃ የተረጋገጠበት ፤ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓቱን የሳይበር ደህንነት እና የማህበረሰቡን የዲጂታል መታወቂያ መብቶች የሚያስጠብቅ የህግ ማዕቀፍ የተዘጋጀለት ፤ ግልፅ፣ ተቋማዊ ሃላፊነቶችና የተጠያቂነት ማዕቀፎች ያሉት ፤ እንዲሁም የነዋሪዎችን ቅሬታ የሚፈታበት አስተማማኝና ገለልተኛ የቅሬታ አፈታት ሥርዓት ያለው መሆን አለበት፤

4/ ወደ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚገቡ ማናቸውም የተመዝጋቢ መረጃዎች በቀጥተኛነት ለስርዓቱ ዓላማ ብቻ የሚያስፈልጉ የተመጠነ መረጃ ማሰባሰብ መርህን የሚከተል መሆን አለበት፤

5/ ተጠቃሚ አካላት የነዋሪ ማንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የዲጂታል መርሃ ግብሮችን በሚዘረጉበት ጊዜ ከዲጂታል መታወቂያ የቴክኖሎጂ ስርዓት እና ከህግ ማዕቀፉ ጋር በተጣጣመ መልኩ መተግበር ይኖርበታል፤

6/ የዲጂታል መታወቂያ መያዝ ወይም የማረጋገጥ አገልግሎት ማግኘት በራሱ የተመዝጋቢ ዜግነትን ወይም ነዋሪነትን ማረጋገጫ አይሆንም፤

7/ የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ምዝገባ በነዋሪው ነፃ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት።

8/ ማንኛውም ነዋሪ ለምዝገባ በሚያመለክትበት ጊዜ ተቋሙ ቀደም ሲል አመልካቹ ዲጂታል መታወቂያ ያልተሰጠው መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት።

## 6. የምዝገባ ስርዓት

መዝጋቢው አካል የተመዝጋቢ የግል መረጃን ለማረጋገጥ የሚያገለግሉ የመታወቂያ ሰነዶች እና ሌሎች በተቋሙ ተቀባይነት ባላቸው ሰነዶች ወይም የሰው ምስክር ማስረጃዎችን በመጠቀም በማረጋገጥ መመዝገብ ይኖርበታል ።

## 7. የግል መረጃ

1/ ወደ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚገባ የግል መረጃ የእያንዳንዱን ተመዝጋቢ የዲሞግራፊክ መረጃ እና ባዮሜትሪክ መረጃን ያካተተ መሆን አለበት፤

2/ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት፡-

ሀ) ስም ፣ የአባት ስም ፣ የአያት ስም ፣ ወይም በዚህ መልክ የተደራጀ ህጋዊ ስም ለሌለው ተመዝጋቢ ተቋሙ ህጋዊ የሆነውን ስያሜ ይመዘግባል፣

ለ) የትውልድ ቀን፣ ወር እና ዓመት፣

ሐ) ፆታ፣

መ) መኖሪያ አድራሻ ፤

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል መረጃን ሳይጨምር የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚከተሉትን መረጃዎች እና ሌሎችም በአማራጭነት ሊይዝ ይችላል ::

ሀ) ዜግነት፣

ለ) ስልክ ቁጥር፣

ሐ) የኢሜይል አድራሻ፣

መ) ፖስታ አድራሻ፣

4/ አንድ ተመዝጋቢ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሰረት የተዘረዘሩ የመታወቂያ ሰነድ ማስረጃዎች ማቅረብ በማይችልበት እና በምስክር በሚመዘገብበት ጊዜ ምስክሩ:-

ሀ) ልዩ ቁጥር ያለው ወይም፣

ለ) በዲጂታል መታወቂያ ስርዓቱ ላይ ለመመዝገብ ባዮሜትሪክ መረጃውን የሰጠ እና በአንቀጽ 6 መሠረት የመታወቂያ ሰነዶችን ያቀረበ መሆን አለበት፣

5/ ስለ ባዮሜትሪክ መረጃ

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀፅ 7 ላይ ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የባዮሜትሪክ መረጃዎች ከማንኛውም ተመዝጋቢ በአስገዳጅነት ይሰበሰባሉ፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ በአካል ጉዳት ምክንያት ተመዝጋቢው ሌሎች ባዮሜትሪክ መረጃ መስጠት አለመቻሉ በተቋሙ ከተረገገጠ፣ ከፊት ገፅታ ፎቶግራፍ ውጪ ሌላ የባዮሜትሪክ መረጃ አስገዳጅ መሆን አይኖርበትም ፤

ሐ) በጤና ሁኔታ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተመዝጋቢዎች ተቋሙ ባዮሜትሪክ መረጃ ለመቀበል በሚችሉበት መልክ ማስተናገድ ይኖርበታል ፤

መ) ባዮሜትሪክ መረጃ ተቋሙ በሚያወጣው የጊዜ ገደብ መሠረት በድጋሚ መታደስ ይኖርበታል።

## 8. ህፃናት የዲጂታል መታወቂያ ስለሚያገኙበት ሁኔታ

ለአካለ መጠን ያልደረሰ ህጻን ፤ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓቱ ላይ በተመዘገበ ወላጅ ፣ አሳዳጊ ወይም ሕጋዊ ሞግዚት በኩል ተመዝግቦ ባዮሜትሪክ መረጃን ያልያዘ የግል መረጃን በማስበመዝገብ የህፃናት ዲጂታል መታወቂያ ሊያገኝ ይችላል።

## 9. ስለ ልዩ ቁጥር

1/ መዝጋቢው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተዘረዘሩትን የተመዝጋቢ መረጃዎች መዝግቦ ወደ ስርዓቱ ካስገባ በኋላ ፣ ተቋሙ አንድ ነዋሪ ከሌላ ነዋሪ በልዩነት እና በአስተማማኝነት ለመለየት የሚያስችል ልዩ ቁጥር ለእያንዳንዱ ተመዝጋቢ መስጠት ይኖርበታል፤

2/ ልዩ ቁጥሩ ኤሌክትሮኒክ በሆነ ስርዓትና በሚስጥራዊ መንገድ የሚመነጭ ሲሆን ከቁጥሩ ጀርባ ያለውን ዝርዝር መረጃ እና ግላዊነት የሚጠብቅ ይሆናል፤

3/ አንድ ልዩ ቁጥር ለአንድ ተመዝጋቢ ብቻ የሚሰጥ ሲሆን ፤ ይህ ልዩ ቁጥርም በቋሚነት ሳይቀየር ከተመዝጋቢው ጋር ይተሳሰራል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ልዩ ቁጥር እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ በተቋሙ አሠራር ለተለያዩ የሥራ ዘርፎች ፣ በተለየ መልኩ ወይም በተመዝጋቢው ፍላጎት ፣ ከልዩ ቁጥር ጋር በሚስጥራዊ ሁኔታ የተያያዙ ፣ የተመዝጋቢን ግላዊነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ፣ የራሳቸው ጊዜ ገደብ ያላቸው ፣ ልዩ ቁጥሩን ተከተው መሥራት የሚችሉ ተለዋጭ ቁጥሮች ማመንጨት ይቻላል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ልዩ ቁጥር የማይለወጥ ሲሆን፣ የተመዝጋቢውን የመረጃ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል በማስረጃ ላይ የሚታተመውና በሌሎች ሁኔታዎች ጥቅም ላይ የሚውለው ቁጥር በተለዋጭ ቁጥር ሊተካ ይችላል ፤

6/ የዲጂታል መታወቂያ ልዩ ቁጥር የጠፋበት ማንኛውም ሰው ልዩ ቁጥሩ ስለመጥፋቱ ለዲጂታል መታወቂያ ተቋም ወይም ተቋሙ ከወከለው አካል በተቋሙ አሰራር መሰረት ቁጥሩን መልሶ ማግኘት ይችላል፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ በተቋሙ አሠራር መሰረት የተመዝጋቢው ሞት ከተረጋገጠ ፤ ተቋሙ ልዩ ቁጥሩ ሳይቀየር እንደፀና እንዲቆይ እና ለማረጋገጥ አገልግሎት ሥራ ላይ እንዳይውል የማድረግ ሃላፊነት ይኖርበታል ፤

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ በተመዝጋቢው ፍላጎት ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የዲጂታል መታወቂያ ልዩ ቁጥር ሊቆለፍ ወይም ከሥራ ውጪ እንዲሆን ሊደረግ ይቻላል ፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ ተቋሙ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

## 10. ስለ ዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ

1/ በዲጂታል መታወቂያ ተቋም እና ውክልና በተሰጣቸው አካላት የሚሰጥ ማንኛውም አይነት የዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት መረጃዎች በሙሉ፣

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 5 (ለ) ላይ ከተጠቀሰው የፊት ገፅታ ፎቶግራፍ፣

ሐ) ልዩ ወይም ተለዋጭ ቁጥር፣

መ) መታወቂያው የተሰጠበት እና የሚያበቃበት ቀን፣እና

ሠ) ሌሎች በአንቀጽ 7 ውስጥ ከተጠቀሱ መረጃዎች ውስጥ በተቋሙ የሚወሰኑ መረጃዎች፤

2/ የዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ ዕድሳት ከባዮሜትሪክ መረጃ የእድሳት ዘመን ጋር አብሮ መሆን ይኖርበታል፤ ሆኖም የዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ እስከሚታደስ ድረስ የዲጂታል መታወቂያ ማረጋገጫ አገልግሎት መስጠት አይቻልም፤

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (2) (ሐ) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ በተቋሙ ወይም ተቋሙ በወከላቸው አካላት ሊሰጥ ይችላል፤

4/ ዲጂታል መታወቂያ ተቋም፣ የዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ በሚያድስበት ጊዜ ቀድሞ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትክክለኛነታቸውን እና የተመዝጋቢውን ማንነት ትክክለኛነት አረጋግጦ የማደስ ግዴታ አለበት፤

5/ ዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ማንኛውም ነዋሪ ፤ መታወቂያው ስለመጥፋቱ የሚገልጽ ማስረጃ ወይም የተበላሸውን መታወቂያ በማያያዝ ፤ በምትኩ ዲጂታል መታወቂያ እንዲሰጠው ለተቋሙ በማመልከት የተቋሙን አሰራር ተከትሎ መውሰድ ይችላል፤

6/ የዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ ወድቆ ያገኘ ማንኛውም ሰው መታወቂያውን ወዲያውኑ ለተቋሙ ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ማስረከብ አለበት።

## 11. ስለ ቋንቋ

1/ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚመዘገቡና በዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ ላይ የሚገለፁ የግል መረጃዎች በፌዴራል መንግሥት የሥራ ቋንቋ ወይም ምዝገባ በሚካሄድበት ክልል የሥራ ቋንቋ እና በእንግሊዝኛ መሆን ይኖርባቸዋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ የግል መረጃም ሆነ በዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ ላይ የሚወጣ መረጃ ተቋሙ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሰረት በተጨማሪ የአገር ውስጥ ቋንቋ ሊመዘገብ ይችላል።

## 12. ስለ ዲጂታል መታወቂያ የመረጃ ለውጥ

ማንኛውም ተመዝጋቢ ወደ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት በገቡ የግል መረጃዎች ላይ ለውጥ ሲኖር የዲጂታል መታወቂያ ለሚሰጠው አካል ማሳወቅ አለበት።

# ክፍል ሶስት

# ስለ ዲጂታል መታወቂያ ተጠቃሚ አካላት እና የማረጋገጥ አገልግሎት

## 13. ስለ ተጠቃሚ አካላት

1/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 7 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ማንኛውም ተጠቃሚ አካል ለነዋሪው ለሚሰጠው አገልግሎት የዲጂታል መታወቂያ እንደ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ የሚያደርግ አሠራር በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ፍቃድ ሊዘረጋ ይችላል፤

2/ ተጠቃሚ አካላት በተመዝጋቢው ፈቃድ ላይ ተመስርተው የግለሰብ ማንነትን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጋቸውን መረጃ ከተቋሙ ወይም ተቋሙ ከወከለው አረጋጋጭ አካል ማግኘት ይችላሉ፤

3/ ማንኛውም ተመዝጋቢ፣ በዲጂታል መታወቂያ ላይ የተመሰረቱ አገልግሎቶችን ማግኘት ሲፈልግ፣ በተጠቃሚ አካላት በኩል የማረጋገጥ አገልግሎት ማግኘት ይችላል፤

4/ ተጠቃሚ አካላት አገልግሎት መስጠት ከመጀመራቸው በፊት ከዲጂታል መታወቂያ ተቋም ደንበኞችን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ለመለየት የሚረዱ መረጃዎች ለማግኘት ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል፤

5/ በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ አካላት የተመዝጋቢ መረጃን ትክክለኛነት ከአረጋጋጭ አካል ማግኘት በማይችሉበት ወቅት ፤ የራሳቸውን ሌላ አማራጭ ተጠቅመው አገልግሎት የመስጠት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

6/ ተጠቃሚ አካላት ከዲጂታል መታወቂያ የማረጋገጥ ስርዓት ያገኙትን መረጃ ይዘው ማቆየት የሚችሉበትን የጊዜ ገደብን በተመለከተ ተቋሙ በመመሪያ ይወስናል፡፡

## 14. ስለ ማረጋገጥ አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም

1/ የዲጂታል መታወቂያ የአንድን ነዋሪ ልዩ ግላዊ ማንነትን ለማስረዳት ወይም ለማረጋገጥ እንደ ህጋዊ እና በቂ ማስረጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፤

2/ የዲጂታል መታወቂያ ተቋም አንዱ አረጋጋጭ አካል ቢሆንም ፤ ተቋሙ በሚሰጠው ውክልና ተጨማሪ አረጋጋጭ አካላትን መሰየም ይችላል፤

3/ ማንኛውም ተመዝጋቢ የዲጂታል መታወቂያ ላይ የተመሠረተ የማረጋገጥ አገልግሎት ለማግኘት ልዩ ቁጥር ወይም ልዩ ቁጥሩን የያዘ የዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

4/ አረጋጋጭ አካላት የግል መረጃን ለተጠቃሚ አካላት በሚያረጋግጡበት ወቅት የአገልግሎት ፍላጎትን መነሻ በማድረግ፣ ተቋሙ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት ፣ ዝቅተኛ ተፈላጊ የግል መረጃዎችን ብቻ መስጠት ይኖርባቸዋል።

5/ አረጋጋጭ አካላት ሆኑ ተጠቃሚ አካላት ከዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ላገኙት የግል መረጃ ተገቢ ጥበቃና ደህንነት  የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

# ክፍል አራት

# የግል መረጃ አስተዳደር፣ ጥበቃ ፣ ደህንነት እና የቅሬታ አፈታት ስርዓት

## 15. የግል መረጃ አስተዳደር

1/ የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የተመዝጋቢ መረጃን በአስተማማኝነት የሚይዝ ጠንካራ መረጃ አስተዳደር ስርዓት መሆን አለበት፤

2/ የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት በጊዜ ሂደት የሚለዋወጡ የዲጂታል መታወቂያ መረጃዎችን የማዘመን፣ እንደገና የማረጋገጥ ፣ የማደስ ፣ በጊዜያዊነት የመቆለፍ ወይም የመሻር ሥራዎችን ይሠራል፡፡

## 16. ስለ መረጃ መጭበርበር ወይም መሳሳት

1/ የአንድ ነዋሪ ዲጂታል መታወቂያ የተጭበረበረ መሆኑ ከተረጋገጠ ፤ ተቋሙ መረጃውን ሊያስተካክል ፣ዲጂታል መታወቂያውን ሊቆልፍ ፣ ወይም የተጭበረበረው መረጃ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ለማድረግ የሚያስችሉ ህጋዊ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሊወስድ ወይም ክስ ሊመሰርት ይችላል፤

2/ ተቋሙ በቸልተኝነትም  ሆነ ሆነ ተብሎ የገባ የተሳሳተ መረጃ መኖሩ ሲያረጋግጥ፣ ልዩ ቁጥሩ ሳይቀየር መረጃውን የማስተካከል ሃላፊነት አለበት።

## 17. የግለሰብ መረጃ አያያዝና ደኅንነት

1/ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የተሰበሰቡ መረጃዎች ከተለያዩ የተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ ፣ የኤሌክትሮኒክ መንገዶችን በመጠቀም ከሚደርሱ ጥቃቶች ፣ ከስርቆት ፣ ከመጭበርበር እና መሰል የወንጀል ጥፋቶች የሚከላከል ደህንነቱ የተጠበቀ የህግና አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት እንዲሁም ጠንካራ የቴክኒክና የደህንነት ስርዓት መተግበር  አለበት፤

2/ ለዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የተሰበሰቡ የግል መረጃዎች ፣ ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ አኳኋን በስርዓት ተደራጅተው ተቋሙ በሚያስተዳድረው የመረጃ ቋት ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።

## 18. የተመዝጋቢ መረጃ ጥበቃ

1/ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የተሰበሰበ ማንኛውም የተመዝጋቢ ግላዊ መረጃ ባለቤት ተመዝጋቢ በመሆኑ ፤ በማንኛውም የዲጂታል መታወቂያ አሠራር ስርዓት ውስጥ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚደረጉ የማረጋገጥ ተግባራት በተመዝጋቢው ፈቃድ  መደረግ አለባቸው፤

2/ ወደ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚገቡ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመመዝገብ፣ በማረጋገጥ እና ይዞ በማቆየት ሂደት ባሉ ተግባራት ውስጥ የተመዝጋቢ መረጃዎች ሚስጢራዊነት የተጠበቀ እንዲሆን  ተቋሙ ማረጋገጥ አለበት፤

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀፅ 4 በተቀመጠው መርህ መሰረት ለዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ፤ ነዋሪዎችን በልዩ ሁኔታ ለመለየት የግዴታ የሚያስፈልጉና ስርዓቱን በቀጥታ ከሚደግፉ በስተቀር ሌሎች መረጃዎች ሊሰበሰቡ አይችሉም፤

4/ ማንኛውም ሰው ተመዝጋቢ ፈቃዱን በግልጽ ሳይሰጥ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የተመዘገቡ የግል መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መግለጽ፣ ማሰራጨት፣ ማተም፣ መጠቀም፣ መረጃውን መስጠት ወይም ቅጂውን ለሶስተኛ ወገኖች ወይም አካላት መስጠት ወይም ይፋ ማድረግ አይቻልም፤

5/ አሰራርና ህግን ጠብቆ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ለተሰበሰበ የማንኛውም ተመዝጋቢ ግላዊ መረጃ ያለ ተመዝጋቢው ፈቃድ ለሌላ ሰው መግለጽ ፣ ማስተላለፍም ሆነ እንዲለወጥ መፍቀድ የተከለከለ ነው፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ የተደነገገው ቢኖርም ፣ በህግ ስልጣን ለተሰጠው ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት የግል መረጃው ለሚመለከተው ህጋዊ አካል ሊገለጽ ወይም ሊተላለፍ ይችላል፡፡

7/ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የተሰበሰቡ ግላዊ መረጃን የማያጋልጡ የተጨመቁ ዲሞግራፊክ ሪፖርቶች እና የስታትስቲክስ መረጃዎችን በህግ ለተፈቀደላቸው አካላት በተቋሙ አሠራር መሰረት ሊሰጡ ይችላሉ፤

8/ ከዲጂታል መታወቂያ ቋት አሠራሩን ጠብቆ ለተጠቃሚ አካላት የተላለፈ የተመዝጋቢ መረጃ የሚያገለግለው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው ለተፈለገው አገልግሎት ብቻ ሲሆን ፤ መጀመሪያ ከተላለፈበት አላማ ባልወጣ መልኩ ተጠቃሚው አካል ይህንን መረጃ በራሱ ቋት ውስጥ ማስቀመጥና ለራሱ አገልግሎት ብቻ መጠቀም ይችላል፤

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ተጠቃሚ አካላት በተመዝጋቢው ፈቃድ ያገኙትን መረጃ ፣ መረጃውን ከወሰዱበት አላማ ውጪ ለራሳቸውም ሆነ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ተግባር ነው፤

10/በምዝገባ ወቅት በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚዘጋጅ የተመዝጋቢውን ሙሉ ፈቃድ ፣ መብት እና ግዴታዎች የሚገልፅ የፈቃደኝነት ቅፅ በተመዝጋቢው መሞላትና መፈረም አለበት፤

11/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ በምዝገባ ወቅት ለተመዝጋቢ ምስክር ሆኖ ለሚቀርብ ሰው ፤ በተቋሙ የሚዘጋጅ የምስክሩን ሙሉ ፈቃድ ፣ መብት እና ግዴታዎች የሚገልፅ የፈቃደኝነት ቅፅ በምስክር መሞላትና መፈረም አለበት ፤ የምስክሩ ልዩ ቁጥር ወይም የምዝገባና የማንነት ማረጋገጫ ሰነዶች በቅጹ ላይ መሞላት እና በዲጂታል መታወቂያ ስርዓቱ ተመዝግቦ መያዝ አለበት፤

## 19. የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት

1/ ተቋሙ የቅሬታ ማስተናገጃ ክፍል ማቋቋም እና ይህንኑ ለተገልጋዮች ይፋ ማድረግ አለበት፤

2/ ማንኛውም ሰዉ በተቀበለው የዲጂታል መታወቂያ አገልግሎትና በተላለፈበት ውሳኔ ላይ ካልተስማማ ለተቋሙ ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው፤

3/ በተቋሙ የአሠራር ስርዓት ሂደት የሚያጋጥሙ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች አቀራረብና አፈታት ሂደት ፤ ተቋሙ በሚዘረጋው የቅሬታ አቀራረብና አፈታት መመሪያ መሠረት ይፈታል፤

4/ በተቋሙ የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ አካል ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፤

# ክፍል አምስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 20. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው የዚህ አዋጅ ዓላማ እንዲሳካ የመተባበር ግዴታ አለበት።

## 21. የተሻሩ ሕጎች

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሠራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 22. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

2/ ተቋሙ ይህን አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ የሚወጣን ደንብ ለማስፈፀም የሚከተሉትን እና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችን አስመልክቶ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፣

ሀ) የዳግም ምዝገባ ቅጣትን በተመለከተ፣

ለ) የተመዝጋቢን የመረጃ ደህንነት ለመጠበቅ የሚቀያየረውን ሚስጥራዊ ተወካይ ቁጥር ሊተካ ስለሚችልበት ሁኔታ፣

ሐ) አንድ ተመዝጋቢ ከሌላ ተመዝጋቢ በልዩነት እና በአስተማማኝነት ለመለየት የሚያስችል ልዩ ቁጥር ስለሚሰጥበት የባዮሜትሪክ መረጃ ይዘት እና ተያያዥ ዝርዝር አሠራሮች፣

መ) ከዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ፣ ማረጋገጥ፣ መጠቀም፣ ማስተዳደር እና ሌሎች አገልግሎቶችን፤ በውክልና ለተጠቃሚ ፣ ለመዝጋቢ እና ለሌሎችም አካላት መስጠት ስለሚቻልበት ዝርዝር ሁኔታዎች፣

ሠ) ለአካለ መጠን ላልደረሰ ህጻን የወላጅ፥ የአሳዳጊ ወይም ህጋዊ ሞግዚት የህፃናት ዲጂታል መታወቂያ ስለሚሰጥበት አግባብ ፣ የእድሜ ገደብ  እና ማረጋገጥ ጉዳዮች፣

ረ) በአካል ጉዳት ምክንያት አንድ ወይም ከአንድ በላይ ባዮሜትሪክ መረጃ መስጠት አለመቻሉ ከተረገገጠ ፣ መውሰድ የሚቻሉት የባዮሜትሪክ መረጃ አሰባበሰብ በሚመለከቱ ጉዳዮች፣

ሰ) በጤና ሁኔታ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ዲጂታል መታወቂያ ተቋም ባዮሜትሪክ መረጃ ለመቀበል በሚችሉበት መልክ የህክምና ማስረጃ ተቀብሎ ፤ ቋሚ ያልሆነ ዲጂታል መታወቂያ ሊሰጣቸው ስለሚችልባቸው ጉዳዮች፣

ሸ) ባዮሜትሪክ መረጃ በድጋሚ መታደስ ስለሚኖርብት የጊዜ ገደብ፣

ቀ) የዲጂታል መታወቂያ በያዛቸው መረጃዎች ወይም ወደ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት በገቡ የግል መረጃዎች ላይ ለውጥ ማሳወቅና መረጃውን ማስተካከል በሚመለከቱ ጉዳዮች፣

በ) የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን አቀራረብና አፈታት በተመለከቱ ጉዳዮች፣

ተ) በዲጂታል መታወቂያ ተቋም እና ውክልና በተሰጣቸው አካላት የሚሰጥ የዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ ስለሚይዛቸው መረጃዎች ፣ አገልግሎት የሚያበቃበት ዘመን እና ሌሎች በምዝገባ ጊዜ የተወሰዱ መረጃዎች ስለሚታተሙበት አግባብ፣

ቸ) የተመዘጋቢዎችን መደበኛ መኖሪያ ቦታ በተመለከተ አካታች እንዲሆን ስለሚወሰንባቸው ሁኔታዎች፣

ነ) በቸልተኝት ወይም ሆነ ተብሎ የገባ የተሳሳተ መረጃ ልዩ ቁጥሩ ሳይቀየር ህጋዊ መንገዱን ተከትሎ መረጃውን ማስተካከል ስለሚቻልበት አግባብ፣

ኘ) ለምዝገባ ስለሚያገለግሉ በተቋሙ ተቀባይነት ያላቸው የፅሁፍ ወይም የሰው ምስክር ማስረጃዎች በተመለከተ እና ወደ ስርዓቱ የሚገቡ የመታወቂያ እና የአድራሻ ማስረጃዎች፣

ከ) ከተለያዩ አካላትና የዲጂታል ስርዓቶች ጋር ስለ መረጃ የማጋራት ፣ የመለዋወጥ እና የማረጋገጥ አግባብ፣

ኸ) ተጠቃሚ አካላት ከዲጂታል መታወቂያ የማረጋገጥ ስርዓት ያገኙትን መረጃ ይዘው ማቆየት የሚችሉበትን የጊዜ ገደብን በተመለከተ፡፡

## 23. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ..... ቀን 2014 ዓ.ም.**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**